ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
መንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት
ሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ
Ethiopian Orthodox Tewahedo Church
Patriarchate Head Office
SUNDAY SCHOOL DEPARTMENT

ቍጥር 44/ገ/ተ/2002
Ref.No.

6-2 ቀን ፪፲ 2002 ዓ/ም
Date ________ 200 ________

በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ መንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት
ሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ሥር
ለማኅበረ ቅዱሳን ጽ/ቤት
<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ፡- <u>የተወሰነውን ውሳኔና መመሪያ ስለማሳወቅ ይመለከታል፤</u>

"በሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያና በመምሪያው ሥር በሚተዳደረው በማኅበረ ቅዱሳን አባላት መካከል የተፈጠረውን የሥራ አለመግባባት ችግር መርምሮ የጋራ መፍትሔን ማስገኘት ይቻል ዘንድ መስከረም 12 ቀን 2002 ዓ.ም ከፍተኛ የሆነ የሰላም ጉባኤ መካሄዱ ይታወቃል።

ይኸው የሰላም ጉባኤ ያስተላለፈው መመሪያ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲተላለፍና በሥራ እንዲተረጐም ለማስቻል ከብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ልዩ ጽ/ቤት በቁጥር ል/ጽ/55/2002 በ29/1/2002 ዓ.ም በተጻፈ ተገልጾልናል።

ስለዚህ የተላለፈውን የሰላም ጉባኤ መመሪያ የያዘ 11 ገጽ አባሪ አድርገን የላክን ስለሆነ በማደራጃ መምሪያው በኩል ለየአህጉረ ስብከቱ እና ለማኅበሩ እንዲሁም ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት ሁሉ እንዲተላለፍና መመሪያው ተጠብቆ እንዲሠራ ጥብቅ ክትትል እንዲደረግ እናስታውቃለን።" በማለት በቁጥር 517/16187/2002 በቀን 3/2/2002 ዓ.ም የተጻፈ መመሪያ ደርሶናል።

በመሆኑም በመተዳደሪያ ደንቡና በተወሰነው ውሳኔ መሠረት ሥራችሁን እንድታከናውኑ እየገለጽን የተወሰነውን ውሳኔ በተግባር ላይ ለማዋል ይቻል ዘንድ ለጊዜው ለሥራው ቅልጥፍና ሲባል

1. ከአዲስ አበባ አንስቶ እስከ አህጉረ ስብከት በማኅበሩ ስም የተከፈቱት የባንክ አካውንት ቁጥር በዝርዝር
2. በማኅበሩ ስም የተከፈቱት ልዩ ልዩ የገቢ ማግኛ ተቋማት እና ቋሚ ንብረቶች በዝርዝር በተቀላጠፈ መንገድ ለማደረጃ መምሪያው እንድታስታውቁ እያስገነዘብን ማደረጃ መምሪያው ማኅበሩ ለሚያቀርባቸው ማንኛውም ጥያቄ ሕገ ደንቡንና ውሳኔውን መሠረት ባደረገ መልኩ ለማስተናገድና ተባብሮ ለመሥራ ዝግጁ መሆኑን እያረጋገጠ ውሳኔውን የያዘ 12 ገጽ ከዚህ ጋር አያይዘን የላክን መሆናችንን እናስታውቃለን።

"ከመንፈሳዊ ሰላምታ ጋር"

ቆሞስ አባ
ሠረቀ ብርሃን ወልደ ሳሙኤል
የሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ
ዋና ኃላፊ
Komos Aba
Sereke birhan Wolde Samuel
Head of Sunday Schools Department

Te. 251-1-56 57 32
251-1-56 72 79 55 00 98 55 00 99 ፖ. ሣ. ቁ. 81286 አዲስ አበባ

<u>ግልባጭ፡-</u>

- ለቅዱስ ሲኖዶስ ጽ/ቤት
- ለብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ልዩ ጽ/ቤት
- ለጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት
- ለፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ጽ/ቤት
- ለአስተዳደር መምሪያ
- ለሊቃውንት ጉባኤ
- ለካህናት አስተዳደር መምሪያ
- ለበጀትና ሂሣብ መምሪያ
- ለቁጥጥር አገልግሎት መምሪያ
- ለሰበካ ጉባኤ ማደራጃ መምሪያ
- ለገዳማት አስተዳደር መምሪያ
- ለሕግ አገልግሎት
- ለስብከተ ወንጌልና ሐ/ተ/መምሪያ
- ለንዋየ ቅድሳት ማደራጃና ምርት ስርጭት መምሪያ
- ለውጭ ጉዳይ መምሪያ
- ለቅርሳ ቅርስ መምሪያ
- ለልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን
- ለሕጻናትና ቤተሰብ አስተዳደር ደርጅት
- ለጎፋ እደ ጥበብ ማሠልጠኛ
- ለዕቅድና ልማት መምሪያ
- ለትንሳኤ ማሳተሚያ ድርጅት
- ለቤቶችና ሕንፃዎች አስተዳደር ልማት ድርጅት
- ለቁልቢ ንዋየ ቅዱሳት ማደራጃ
- ለቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ
- ለሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ መንፈሳዊ ኮሌጅ
- ለቅዱስ ፍሬምናጦስ አባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን መንፈሳዊ ኮሌጅ <u>አዲስ አበባ</u>
- ለቅዱስ ፍሬምናጦስ አባ ሠላማ ከሣቴ ብርሃን መ/ኮሌጅ <u>መቀሌ</u>
- ለሁሉም አኅጉረ ስብከቶች
- ለሚመለከታቸው መሥሪቤቶች ሁሉ <u>በያሉበት</u>

ቁጥር 517/6187/2002
Ref. No.

3/2 ቀን ፲፱፻፳፪/፺
Date 200

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
**መንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት**
Ethiopian Orthodox Tewahedo Church
**PATRIARCHATE HEAD OFFICE**

በጠቅላይ ቤተ ክህነት
ለሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ
አዲስ አበባ፤

በሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያና በመምሪያው ሥር በሚተዳደረው በማህበረ ቅዱሳን አባላት መካከል የተፈጠረውን የሥራ አለመግባባት ችግር መርምሮ የጋራ መፍትሔን ማስገኘት ይቻል ዘንድ መስከረም 12 ቀን 2002 ዓ.ም. ከፍተኛ የሆነ የሰላም ጉባኤ መካሄዱ ይታወቃል፡፡

ይኸው የሰላም ጉባኤ ያስተላለፈው መመሪያ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲተላለፍና በሥራ እንዲተረጐም ለማስቻል ከብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ልዩ ጽ/ቤት በቁጥር ል/ጽ/55/2002 በ29/1/2002 በተጻፈ ተገልጾልናል፡፡

ስለዚህ የተላለፈውን የሰላም ጉባኤ መመሪያ የያዘ 11 ገጽ አባሪ አድርገን የላክን ስለሆነ በማደራጃ መምሪያው በኩል ለየአህጉረ ስብከቱ እና ለማኅበሩ እንዲሁም ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት ሁሉ እንዲተላለፍና መመሪያው ተጠብቆ እንዲሠራ ጥብቅ ክትትል እንዲደረግ እናስታውቃለን፡፡

ከመንፈሳዊ ሰላምታ ጋር

[Stamp: የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን / Ethiopian Orthodox Tewahedo Church / Patriarchate Head Office / መንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት]

[signature]

ንቡረ እድ ኤልያስ አብርሃ
የጠቅላይ ቤተ ክህነት
ምክትል ሥራ አስኪያጅ
Nbure Eid Alias Abrha
Deputy Manager of the Ethiopian
Orthodox Tewahido Church

ግልባጭ፤
ለቅዱስ ሲኖዶስ ጽ/ቤት
ለብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ልዩ ጽ/ቤት
ለፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስትር
ለአስተዳደር መምሪያ
ለሊቃውንት ጉባኤ
ለካህናት አስተዳደር መምሪያ
ለበጀትና ሂሣብ መምሪያ
ለቁጥጥር አገልግሎት መምሪያ
ለሰበካ ጉባኤ ማደራጃ መምሪያ
ለገዳማት አስተዳደር መምሪያ
ለሕግ አገልግሎት
ለስብከተ ወንጌልና ሐ/ተ/መምሪያ
ለንዋየ ቅድሳት ማደራጃና ምርት ስርጭት መምሪያ
ለውጭ ጉዳይ መምሪያ
ለቅርሳቅርስ መምሪያ
ለልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን
ለሕጻናትና ቤተሰብ አስተዳደር ድርጅት
ለጐፋ እደ ጥበብ ማሠልጠኛ
ለዕቅድና ልማት መምሪያ
ለትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት
ለቤቶችና ሕንፃዎች አስተዳደር ልማት ድርጅት
ለቁልቢ ንዋየ ቅድሳት ማደራጃ
ለቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ
ለሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ መንፈሳዊ ኮሌጅ
ለቅዱስ ፍሬምናጦስ አባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን መንፈሳዊ ኮሌጅ
አዲስ አበባ፤

[handwritten notes] 3/2/02



የመልእክት ሣጥን ቁጥር ፩ሺ፪፻፹፫
P. O. Box 1283
TEL. 011 1 55 00 98, 0111 55 00 99
አዲስ አበባ
ADDIS ABABA
FAX. 57 46 14

አባ ጳውሎስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ
ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ፣
ሊቀ ጳጳስ ዘአኵሱም፣
ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት፣
የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት፣
የዓለም ሃይማኖቶች ምክር ቤት
ለሰላም የክብር ፕሬዚዳንት

**ABBA PAULOS I**
Patriarch of Ethiopia, Archbishop of Axum,
Echegue of the See of St. Tekle Haimanot,
President of WCC and Honorary President of
World Religions for Peace

ቁጥር ል/ፓ/55/2002
Ref. No.

እጅግ አስቸኳይ
Very Urgent

ቀን 27/01/2002 ዓ.ም
Date

ለመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት
አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- መስከረም 12 ቀን 2002 ዓ.ም. በተደረገው ስብሰባ የሰላም ጉባኤ የወሰነውን ስለማስተላለፍ፡፡

በጠቅላይ ቤተ ክህነት የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያና በመምሪያው ሥር በሚተዳደረው በማኅበረ ቅዱሳን አባላት መካከል የተፈጠረውን የሥራ አለመግባባት ችግር መርምሮ የጋራ መፍትሔን ማስገኘት ይቻል ዘንድ መስከረም 12 ቀን 2002 ዓ.ም. ክፍተኛ የሆነ የሰላም ጉባኤ መደረጉ የሚታወስ ነው፡፡

የሰላም ጉባኤ ያሳለፈውን ጽንሰ ሐሳብ ነጥብ የዘገበው መግለጫ በዕለቱ በመገናኛ ብዙኃን መተላለፉ ቢታወቅም፣ ጉባኤው የተወያየንበትን ዝርዝር ነጥብ የያዘው ቃለ ጉባኤ በሥራ ይተረጐም ዘንድ እንዲደርሳችሁ ማድረግ አስፈልጓል ፡፡

ስለዚህ ከፍ ብሎ በተጠቀሰው ቀን በተደረገው የሰላም ጉባኤ የተላለፈውን 11 ገጽ ውሳኔ የዚህ ደብዳቤ አባሪ በማድረግ የላክን ስለሆነ፣ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ያለውን ሁኔታ በመረዳት የበኩላቸውን ድርሻ እንዲፈጽሙ ሆኖ በየሥልጣን ተዋረዱም የቤተ ክርስቲያኒቱ የቅርብ ተጠሪ መሥሪያ ቤቶች ውሳኔውን በሥራ እንዲተረጐሙ ታደርጉ ዘንድ እናስታውቃለን ፡፡

እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ

አባ ጳውሎስ (ፓ/ር)
ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ
ሊቀ ጳጳስ ዘአኵሱም
ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት
የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት
የዓለም ሃይማኖቶች ምክር ቤት ለሰላም የክብር ፕሬዚዳንት
ABBA PAULOS (Dr.)
Patriarch of Ethiopia
Archbishop of Axum
Echegue of the See of St. Tekle Haimanot
President of WCC and
Honorary President of World Religions Conference for Peace

መንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት

ግልባጭ
ለቅዱስ ሲኖዶስ ጽ/ቤት
አዲስ አበባ

51-111-111989, 251-111-550577,
51-111-565747, 251-111-551013
Fax:- 251-111-552211
✉ 1283 አዲስ አበባ Addis Ababa
E-mail: aba.paulos.patriarch@ethionet.et
abagerima@yaho.com

## የሰላም ጉባኤ ስብሰባ

- ስብሰባ የተደረገው በአዲስ የመንበረ ፓትርያርክ ሕንፃ አዳራሽ፤
- ስብሰባ የተደረገበት ዕለት መስከረም 12 ቀን 2002 ዓ.ም.
- የስብሰባው ሰዓት ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት ጀምሮ እስከ 11፡30 ሰዓት

## በስብሰባው የተገኙ አባላት፤

- ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ
  ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም
  ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት የዓለም አብያተ
  ክርስቲያናት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት የዓለም ሃይማኖቶች
  ምክር ቤት ለሰላም የክብር ፕሬዚዳንት የጉባኤው .......................... ሰብሳቢ
- ብፁዕ አቡነ በርተሎሜዎስ ሊቀ ጳጳስ
  የሊቃውንት ጉባኤ የበላይ ኃላፊ .................................................. አባል
- ብፁዕ አቡነ ገብርኤል ሊቀ ጳጳስ
  የሰዋስወ ብርሃን ቅ/ጳ/መ/ኮሌጅ የበላይ ኃላፊ ................................ ››
- ብፁዕ አቡነ ገሪማ
  የብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ልዩ ጽ/ቤት
  የውጭ ግንኙነት የበላይ ኃላፊ፤የዓለም አብያተ ክርስቲያናት
  ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ቢሮ ዋና ጸሐፊ፣ የልማትና ክርስቲያናዊ
  ተራድኦ ኮሚሽን ሊቀ ጳጳስ ....................................................... ››
- ብፁዕ አቡነ ቶማስ
  የአዊ ዞን ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ................................................ ››
- ብፁዕ አቡነ ቀውስጦስ
  የሰሜን ሸዋ ሰላሌ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ....................................... ››
- ብፁዕ አቡነ አረጋዊ ሊቀ ጳጳስ
  የመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል የበላይ ኃላፊ ................. ››
- ብፁዕ አቡነ ይስሐቅ
  የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅና
  የባሌ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ .................................................... ››
- ብፁዕ አቡነ ፊልጶስ
  የኢሉባቦርና ጋምቤላ አህጉረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ፣
  የቤተ መጻሕፍት ወመዘክርና
  የትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት የበላይ ኃላፊ ................................ ››
- ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ
  የምሥራቅ ሸዋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ........................................ ››
- ብፁዕ አቡነ ኤርምያስ ሊቀ ጳጳስ
  የመንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ገዳም የበላይ ኃላፊ .... ››
- ብፁዕ አቡነ ኤጲፋንዮስ
  የምዕራብ ሸዋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ........................................ ››

- ብፁዕ አቡነ ሙሴ
  የደቡብ ምዕራብ ሸዋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ........................................ አባል
- ብፁዕ አቡነ ስምዖን ሊቀ ጳጳስ
  የታዕካ ነገሥት በዐታ ለማርያምና
  የመንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤል ገዳማት የበላይ ኃላፊ ............ ››
- ብፁዕ አቡነ ሕዝቅኤል
  የከፋ ቦንጋና ቤንች ማጂ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ........................ ››
- ብፁዕ አቡነ ዳንኤል
  የምሥራቅ አፍሪካ አህጉረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ .................................. ››
- ብፁዕ አቡነ ሚካኤል
  የሰሜን ምዕራብ ትግራይ ሽሬ እንዳሥላሴ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ... ››
- ብፁዕ አቡነ ሰላማ
  የአኩስምና ማዕከላዊ ዞን ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ............................ ››
- ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ
  በክልል ትግራይ የምሥራቃዊ ዞን አዲግራት ሀ/ስብከት ሊቀ ጳጳስ...... ››
- ብፁዕ አቡነ ማቴዎስ
  የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊና የዋግ ሕምራ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ .. ››

በአንድነት ሆነው ስብሰባን አድርገዋል ።

## ጉዳዩ የሚመለከታቸው የመንግሥት ተጠሪዎች፤

1. ክቡር አቶ ዓባይ ፀሐዬ
   የጠቅላይ ሚኒስቴሩ ብሔራዊ የደኅንነት አማካሪ ሚኒስትር
2. ክቡር ዶክተር ሺፈራው ተክለማርያም
   የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ሚኒስትር
3. ክቡር አቶ መረሳ ረዳ
   በፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር የሃይማኖትና እምነት ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በታዛቢነትና በተመልካችነት ተገኝተዋል ።

እንዲሁም የጠቅላይ ቤተ ክህነት ምክትል ሥራ አስኪያጅ ንቡረ እድ ኤልያስ አብርሃ፤ የየመምሪያውና የየድርጅቶች ኃላፊዎችና የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት የሥራ ኃላፊዎች በጉባኤው ስብሰባ ላይ ተገኝተዋል ።

በተለይም የጉዳዩ ባለቤቶች የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ኃላፊዎች የጉባኤ ተሳታፊዎች በመሆን ቀርበዋል ።

እንደዚሁ ሁሉ ከማኅበረ ቅዱሳን አባላት መካከል የማኅበሩ መሪዎች የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴና ሌሎች ጥሪ የተደረገላቸው አባላት የጉባኤው ተሳታፊዎች በመሆን ተገኝተዋል ።

## የስብሰባው አጀንዳ

በጠቅላይ ቤተ ክህነት የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያና በመምሪያው ሥር በሚተዳደረው በማኅበረ ቅዱሳን አባላት መካከል የተፈጠረውን የሥራ አለመግባባት ችግር መርምሮ የጋራ መፍትሔን ለማስገኘት የተደገረ ስብሰባ ነው ።

ስብሰባው በብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ጸሎተ ቡራኬ ከተከፈተ በኋላ ቅዱስነታቸው የማኅበሩን አላማና ተግባር መሠረት ያደረገ ሰፋ ያለ መመሪያን ሰጥተዋል። ከተሰጡት የመመሪያ ነጥቦች መካከል ቀጥሎ ያለው ተመዝግቧል ።

## ቅዱስነታቸው የሰጡት መመሪያ

በቤተ ክርስቲያኒቱ ማዕከላዊ አስተዳደር ሥር ከሚንቀሳቀሱት መምሪያዎች መካከል የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ በመባል የሚታወቀው መምሪያ ከፍተኛ ድርሻ ያለው የመሥሪያ ቤቱ አካል ነው ።

ከማዕከል እስከ አህጉረ ስብከት ያሉት የኢጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት የሰንበት ትምህርት ቤቶች እየተደራጁ ተልእኮአቸውን የሚያከናውኑት በቃለ ዓዋዲውና በዚሁ የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ በኩል እየታቀደ፤ እየተጠናና እየተወሰነ በሚተላለፈው አመራር መሠረት መሆኑም ተረጋግጧል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ሁለተኛው የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ይህን የወጣቶች ማደራጃ መምሪያ ሲመሠርቱ ወላጆችና ልጆች ተገናኝተው ስለቤተ ክርስቲያናቸው ዕድገትና ስለእምነታቸው ጽናት እየተማሩ፤ እየተመካከሩና እየተወያዩ ሰላማዊ የሆነውን ሥራ በመረዳዳት እየሠሩ እንዲደራጁ ለማድረግ በማሰብ ነበር ።

ከላይ የተመለከተውን ዓላማ በሥራ ለመግለፅ የተመሠረተው ይህ የወጣቶች ማደራጃ መምሪያ ደረጃ በደረጃ እያደገና ዕውቅናም እያገኘ የመምጣቱን ያህል የተለያዩ ማኅበራትም በመምሪያው የበላይ ኃላፊነት ተደራጅተው ሲንቀሳቀሱ ይታያሉ ።

ለማስረጃም ያህል ያለውን ሁኔታ በመመልከት መፍትሔን ማስገኘት ያስቻለን ዘንድ ለዛሬው ስብሰባ ምክንያት የሆነውና ማኅበረ ቅዱሳን በመባል የታወቀው ማኅበር፤ የዚሁ የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ቅርንጫፍ አካል ነው ።

በቅዱስ ሲኖዶስ በጸደቀው መተዳደሪያ ደንብ እንዲተዳደር የተደረገው ማኅበረ ቅዱሳን የደንቡ ተርጓሚና አስፈጻሚ ከሆነው የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ጋር ተጣጥመው ለመሥራት ባለመቻሉ ብዙ ጊዜ ሲጻጻፉ እናያለን ።

ወጣቶች በማዕከል እንዳይሰባሰቡ ተደርጎ የነበረበት ወቅትና ጊዜ አልፎ አሁን በደረስንበት ንቃተ ኅሊና ተደራጅተን ስለቤተ ክርስቲያናችን ዕድገትና ዘላቂ ሕይወት መወያየት ይጠበቅብናል ምክንያቱም በክብ ጠረጴዛ ተቀራርቦ መወያየትና መተራረም ለችግሮቹ ሁሉ መፍትሔን የሚያስገኝ በመሆኑ ነው ።

ማኅበረ ቅዱሳን ከመተዳደሪያ ደንቡ ውጭ ወጣ ያለ ዓላማ እንዳለው ስለሚነገር ቀኖናውን ተከትለን እየተመካከርን መሥራት አለብን አንድነትና ኅብረት ከሌለን ብዙ እንቅፋት ሊፈጠር ይችላል ።

ይህ አዲስ ዓመት ለሥራችን ሁሉ በር ከፋች በመሆኑ ከሕግ የወጣ ያፈነገጠ ቢኖር አስተካክለን አንድነትን፤ ግልፅነትንና ተጠያቂነትን ማዕከል ያደረገ ሥራ እየሠራን፤ እየተመካከርንና እየተደማመጥን ከተሰጠን የኃላፊነት ድርሻ ሳንወጣ ለአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን በጋራ መሥራት አለብን ይህን ለመፈጸምና ለማስፈጸም እንድንበቃ እግዚአብሔር አምላካችን ይርዳን በማለት ንግግራቸውን ደምድመዋል ።

በሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያና በማኅበረ ቅዱሳን የሥራ አፈጻጸም ግድፈት መነሻነት የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ያሰማው ቅሬታና ሮሮ በዚህ ጠባብ አገላለፅ ሊጠቃለል የማይችል ቢሆንም ከዘርፈ ብዙ ችግር ጥቂቱን ክፍል እንደማስረጃ ጠቅሶ ማለፍ አስፈልጓል ።

## ከማደራጃ መምሪያው የቀረበ

ማኅበረ ቅዱሳን በተሰጠው መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ከሃይማኖት አባቶችና ከሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ጋር በመመካከርና አመራር በመቀበል መሥራት ሲገባው ሁሉንም ወደጎን በመተው፤

- በአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት በወረዳ ቤተ ክህነትና በሀገረ ስብከት ሥራ ጣልቃ እየገባ ምሥጢሩ ያልገባቸውን ንዑሐን ወጣቶች በማነሣሣት ሰላም የሚነሣ ችግር እንዲፈጠር ማድረጉ፤
- ማኅበሩ በኢትዮጵያ ቅዱስ ሲኖዶስ ሥር ሆኖ መንቀሳቀስ ሲገባው በውጭ ዓለም ከሚገኙ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስና የቅዱስ ፓትርያርኩን አመራር ከማይቀበሉ አባላት ጋር ሆኖ በመሥራት ላይ የሚገኝ መሆኑ፤
- የማኅበሩ ግንኙነት ከሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ጋር መሆኑ እየታወቀ ደንቡን በመጣስ በራሱ ማኅተም ከጠቅላይ ቤተ ክህነት ጀምሮ እስከ ቅዱስ ሲኖዶስና ቅዱስ ፓትርያርክ፤ እንዲሁም እስከ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ከዚህም ሌላ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በመጻጻፍ መዋቅሩ እንዲጣስ መደረጉ፤
- ሐመር፤ ስምዐ ጽድቅ የተባሉ መጽሔቶችና ጋዜጦች በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት ማደራጃ መምሪያው ሳይመለከታቸው ማሳተሙ አግባብ እንዳልሆነ ቢጠየቅም መመሪያውን ለመቀበል ፈቃደኛ አለመሆኑ፤
- በቤተ ክርስቲያኒቱ ማዕከላዊ አስተዳደር በታተመ የገቢና የወጪ ካርኒ ለመሥራት ፈቃደኛ አለመሆኑ፤ አዲት እንዲደረግ ሲጠየቅም ፈቃደኛ ሆኖ አለመገኘቱ፤
- በማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ የተቀመጠውን የመዋቅር ሰንሰለት ሳይጠብቅና አመራር ሰጭ የሆነውን የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያን

... Patriarchate ...

የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት

ሳያስፈቅድ ኃላፊዎችን እያሳሳተ ከሦስተኛ ወገን ጋር በመጻጻፍ ከደንቡ ውጭ መንቀሳቀሱ፤

- የማኅበሩ ያገቢ ምንጭ የሆኑ ተቋማት ከግብር ክፍያ ነፃ ይሆኑ ዘንድ በቤተ ክርስቲያን ስም በመጻጻፍ ላይ የሚገኝ መሆኑ፤
- ደጀ ሰላም በተባለው ድኅረ ገጽ ጁላይ 9/2009 ዓ.ም. ባወጣው ጽሑፉ ብፁዓን አባቶችን መወረፉ፤
- በአጠቃላይም ማኅበረ ቅዱሳን ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ አስተዳደርና ፖለቲካዊ አካሔድ የሚታይበት ተፅዕኖ በማድረስ ላይ እንደሚገኝ በአስረጅነት ከቀረቡት ሠነዶች ላይ ማረጋገጥ ተችሏል ።

ከዚህ በኋላ ግልፅ ውይይት ተካሒዶ ለመፍትሔ በሚበቃ ውሳኔ ላይ መድረስ ያስችለው ዘንድ ጉባኤው የተሠየመበትን ተግባር በመቀጠል በማኅበረ ቅዱሳን በኩል ተፈጽሟል ስለሚባለው የሥልጣን ተዋረድ መጣስ ጉዳይ፤ ከሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ኃላፊዎች በጥቅልና በዝርዝር በቀረቡት ነጥቦች ጉባኤው ተወያይቶበታል ።

እንደዚሁ ሁሉ የማኅበረ ቅዱሳን የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት ባገኙት መድረክ በመጠቀም ከሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ከተሰጠው አመራርና በቅዱስ ሲኖዶስ ከተፈቀደው መተዳደሪያ ደንብ ውጭ የተፈጸመ ስሕተት አለመኖሩን፣ ጥፋት አለ ከተባለም መታረም እንደሚቻል አብራርተዋል ።

አባላቱ ለተነገረባቸው የሥራ ግድፈት የተሰማቸውን ቅሬታ በመግለፅ ቀጥሎ ያለውን ቃል አስመዝግበዋል ።

## ከማኅበረ ቅዱሳን አባላት የቀረበ

ማኅበሩ በቅዱስ ሲኖዶስ ፈቃድና ውሳኔ መሠረት የሚተዳደርበት መመሪያ ተዘጋጅቶለት በጸደቀው መተዳደሪያ ደንብ በመታገዝ የሚሠራ ማኅበር ነው ። እኛም የማኅበሩ አባላት በ1994 ዓ.ም. ተሻሽሎ በወጣው መተዳደሪያ ደንብ መሠረት በአባቶቻችን ሥር ሆነን እየሠራን ብዙ ዓመታትን አስቆጥረናል፤ የማኅበሩ የበላይ ተጠሪ የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ሲሆን አሁን ያሉት የመምሪያው ኃላፊ ከመጡበት ጊዜ ጀምሮ ግን ችግሮች እየተከሰቱ ይታያሉ ።

የማኅበሩን ዝርዝር ሁኔታ ለማስረዳት ብንሞክርም ቀደም ሲል አውቀዋለሁ በማለታቸው ጠለቅ ብለው ሥራችንን ሊረዱልን አልቻሉም፤ ከጥቂት የቆይታ ጊዜ በኋላ በተለያየ ምክንያት የመጻጻፍ ተግባር ሲከሰት ተቀራርበን ለመነጋገር ሙከራ አድርገን ነበር፤ ሆኖም ሊሳካ አልቻለም፤ ከዚህም የተነሣ ግንኙነታችንን ከጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤትና ከብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ልዩ ጽ/ቤት ጋር ማድረግ ግዴታ ሆነብን፤ አሁን እየተሠራ ያለውን ሕንፃ በተመለከተም የሕንፃው ሥራ የተጀመረው ከጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት ባገኘነው ፈቃድ መሠረት ነው፤ ቤቱንም ለመግዛት የቻልነው እንደዚሁ በቤተ ክህነቱ ፍቃድ መሆኑ ታውቋል፤ የማኅበሩ ንብረትና ሕንፃ የቤተ ክርስቲያናችን አንጡራ ሀብት እንጂ የማንም ሊሆን አይችልም ።

በዚህ መሠረት ከመተዳደሪያ ደንባችን ሳንወጣ ከመደበኛው ሥራችን ውጭ በትርፍ ጊዜያችን ጭምር እየተሰባሰብን ቤተ ክርስቲያኒቱን መምህራንን፣ ደቀ መዛሙርትንና ችግረኞችን በመርዳት ላይ እንገኛለን! ምናልባት በመተዳደሪያ ደንባችን ላይ ችግር አለ ከተባለ ሊታረም ይችላል ።

የማኅበሩን የኅትመት ስርጭት በተመለከተም የሀገሪቱንም ሆነ የቤተ ክርስቲያኒቱን ክብር በሚነካ መልኩ ተዘጋጅቶና ተመዝግቦ የተላለፈ ጋዜጣም ሆነ መጽሔት ሌላም ጽሑፍ ቢሆን ያለ አይመስለንም! የቀረጥ ክፍያን በተመለከተም ቤተ ክርስቲያኒቱ እንድትከፍል ከተወሰነ አፈጻጸሙ ማኅበሩን የሚመለከት ይሆናል፤ የማኅበሩ ገንዘብና ንብረት በዋናው መሥሪያ ቤት ኦዲተር ይመርመር የመባሉም ጥያቄ ጉዳይ በማኅበሩ ዘንድ ተቀባይነት አለው፤ ከዐርባ ሺህ ባላነሰ ቁጥር አባላቱን አስመዝግቦ እንደሚንቀሳቀስ የገለፀው ማኅበረ ቅዱሳን መታየቱና መገምገም የሚፈልግ በመሆኑ ለግምገማ ተግባር የተደረገውና የሚደረገው ስብሰባ ሁሉ የሚደገፍ ነው ።

ማኅበሩ በየዐራት ዓመቱ የሚለዋወጥ የመሆኑን ያህል አሁን ያለው አመራር አዲስ ስለሆነ የመሥሪያ ቤቱን ድጋፍ በእጅጉ ይፈልጋል፤ ማኅበሩ ለቅዱስ ፓትርያርኩ ያለው አቋም የማያወላውል ቢሆንም በቤተ ክህነት መሥሪያ ቤትና በሌሎች አህጉረ ስብከት ኋላ ቀር የሆኑ አሠራሮች ይታያሉ፤ እነዚህ ሁሉ በቀልጣፋ አሠራር ተተክተው መሻሻል አለባቸው የሚል አቋም አለን በማለት የማኅበረ ቅዱሳን አባላት የበኩላቸውን ቅሬታ አሰምተዋል ።

ጉዳዩን የሚከታተሉ የጉባኤው አባላትም የበኩላቸውን አስተያየት ለግሰዋል ።

## የጉባኤው አስተያየት

በሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያና በማኅበረ ቅዱሳን አባላት መካከል የተከሰተው ችግር የውስጥ ችግር እንጂ የውጭ አይደለም፤ ችግሩን እያጣበቡ መሔድ ከተቻለ የሰመረ ውጤት ማስገኘት ይቻላል ። ማኅበሩ በቅዱስ ሲኖዶስ ጸድቆ በተላለፈው ደንብ ከተመራ ከበላይ አካላት የሚተላለፍለትን መመሪያ ከተቀበለ ግጭት ሊፈጠር አይችልም፤ የማኅበሩ አባላት ሞያቸውንና ዕውቀታቸውን በቅንነት እንዲያበረክቱ በሚል ታስቦ የተቋቋመ ማኅበር እንደመሆኑ መምሪያውና ማኅበሩ ደረጃቸውን ጠብቀው አቅማቸውን ፈትሸው መራመድ አለባቸው፤ የማኅበሩ አባላት እራሳቸውን የሚመረምሩበት ሁኔታ መፈጠር አለበት፤ በመሥሪያ ቤቱም በኩል የግዴለሽነት አሠራር ሳይኖር ተባብሮ መሥራትና ማሠራት ይጠበቅበታል፤ የተከሰተው ችግር በክቡራን ሚኒስትሮች ታዛቢነትና ተመልካችነት እንዲታይ በመደረጉ ደስታ ተሰምቶናል በእርግጥ እርማት ያልተደረገለት ጋዜጣና መጽሔት እየወጣ ኅብረተሰቡን እያተራመሰ የሚታይ ቢሆንም፤ ስህተታችንን ካላወቅን ሀገርን፤ ቤተ ክርስቲያንን ልንመራ አንችልም። ማኅበረ ቅዱሳንን በተገቢው መንገድ አልተቆጣጠርነውም ተቆጣጥረነው ቢሆን ኖሮ አሁን የተከሰተው ችግር መድረስ ባልቻለም ነበር ። ኅትመቶቹ ሁሉ በሊቃውንት እየተፈተሹ መውጣት ይኖርባቸዋል ። ሳናስበበት በመቅረታችን እንጂ ቀደም ሲል በወጡት ኅትመቶች ላይ መነጋገር ነበረብን ተወያይተን ለችግሮች መፍትሔ

የምናስገኝበትን አጀንዳ ሳናዘጋጅ በመቅረታችን ስህተቶች እየጎሉ ይታያሉ፤ እንደ መፍትሔ ከተያዘው ጠቅላላ ሁኔታ በማኅበራት ስም የተደራጁትን ክፍሎች በተመለከተ እየተጠና ያለው መተዳደሪያ ደንብ ተጠናቆ በሚወጣበት ጊዜ ማኅበረ ቅዱሳንን ሊያካትት እንደሚችል ታምኖበታል፤ ወደፊት በሚወጣው ደንብ የሀብትና ንብረት አወራረስ ጉዳይ ሁሉ በድንጋጌው ሊቀመጥ ይገባል።

በ1994 ዓ.ም. የማኅበሩ ደንብ ሲጸድቅ የተቃወሙ አባቶች ነበሩ፤ የማኅበሩ አባላት ቁጥር እየበዛ ከመታየቱ የተነሣ ማኅበሩ ይፍረስ መባሉ ተገቢ ስለማይሆን መተዳደሪያ ደንቡ ይጽደቅላቸው ተብሎ ተላልፎአል፤ ሆኖም ግን ያልተፈቀደላቸው ሰባክያን እንዳይሰብኩ ያልተፈቀደላቸውን የተለያዩ ኅትመቶችን እንዳያሰራጩ ቅዱስ ሲኖዶስ ወስኖ ነበር፤ ይሁንና ውሳኔው እስካሁን ድረስ አልተከበረም በማለት አስተያየታቸውን ሰጥተዋል ።

በታዛቢነትና በተመልካችነት በጉባኤው ስብሰባ ላይ የተገኙት፤

1ኛ. ክቡር አቶ ዓባይ ፀሐዬ
2ኛ. ክቡር ዶክተር ሺፈራው ተክለ ማርያም፤
3ኛ. ክቡር አቶ መረሳ ረዳ

ከግራቀኙ ተከራካሪዎች የቀረበውንና ከጉባኤው አባላት የተሰጠውን አስተያየት ካዳመጡ በኋላ የሚከተለውን መመሪያ ሰጥተዋል ።

## ከክቡራን ሚኒስትሮች የተሰጠ መመሪያ፤

ማኅበሩ በመንፈሳዊና በልማት ሥራ እየሠራ እንደሆነ እናምናለን፤ ነገር ግን በስምዐ ጽድቅ ጋዜጣና በሐመር መጽሔት የሚተላለፉ አንዳንድ መልእክቶች መንግሥትንና ቤተ ክርስቲያንን፤ መንግሥትንና ሕዝብን የሚያጋጩና ቅራኔን የሚፈጥሩ እየሆኑ ይስተዋላሉ፤ ስለዚህ መታረምና መስተካከል አለባቸው ማኅበረ ቅዱሳን ከቤተ ክርስቲያንና ከመንግሥት እይታ ውጭ እየሔደ የሚታይ ቢሆንም ችግሩ በሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያና በማኅበረ ቅዱሳን መካከል ነው በማለት ብቻ መታለፍ የለበትም ።

ማኅበሩ ሃይማኖትንና ፖለቲካን እያጣመረ የሚሔድ መሆኑን የሚያስገነዝብ መረጃ የተገኘበት ስለሆነ በፈጸመውና በሚፈጽመው ስህተት ሁሉ ሕገ መንግሥቱ በሚፈቅደው መሠረት ለሕግ አቅርቦ አስፈላጊውን ውሳኔ እንዲያገኝ ማድረግ ይቻል ነበር፤ ሆኖም ከአባቶቻችንና ጉዳዩ ከሚመለከተው ጋር በመሆን በጉዳዩ ዙሪያ መወያየት አስፈላጊ ነው የሚለውን ቀና አስተሳሰብ ይዘን ቀርበናል፤ በስብሰባ የሚካሔደው ውይይት እንደፍርድ ቤት ዓይነት ክርክር ሳይሆን ሰላምንና ፍቅርን መተማመንን የሚያመጣ መሆን ይኖርበታል ።

ማኅበሩ ማስተማር የነበረበት ስለ እምነቱ ነው የፖለቲካ ማኅበር ነኝ የሚል ከሆነ የፖለቲካ የሥራ ፈቃድ ማውጣት አለበት፤ ሃይማኖትንና ፖለቲካን ሁለቱን

ጣቀሱ መሔድ ግን አይቻልም ስህተትን በስህተት ማረም የለብንም፤ የተፈጸመው ህተት በሰላማዊ ምክክር መፈታት አለበት ከአሁን በኋላ በሚሰጠው ምክርና በቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ መሠረት መፈጸም አለበት መንግሥትንና ሕዝብን ቤተ ክርስቲያንንና መንግሥትን የሚያጋጭና የሚያለያይ አካሔድ መቃረም ይኖርበታል በማለት አመራር ሰጥተዋል ፡፡

- ማኅበረ ቅዱሳን እያሳተመ በሚያሰራጫቸው የኅትመት ጽሑፎች፤
- በንብረት አጠባበቅ፣ በገንዘብ አሰባሰብና አወጣጥ ተግባር፣
- በአዝ ሰንሰለት አለመጠበቅና በመሳሰለው የሥራ አፈጻጸም የአሠራር ስህተት ተከስቶ እንደነበር፤ አሁን ግን መስተካከል እንዳለበት ሁሉችም የጉባኤው ተሳታፊዎች የየበኩላቸውን አስተያየት ሰጥተዋል።

በታዛቢነትና በተመልካችነት የተሠየሙት ክቡራን ሚኒስትሮችም የሰጡትን አስተያየት በተመለከተ ይህ ከፍተኛ ጉባኤ በዘርፈ ብዙ ችግሮች ላይ ተወያይቶ ከአንድ ዓይነት መፍትሔ ላይ ካልደረሰ ድካማችን ከንቱ ይሆናል፤ የጉባኤው አስተያየት ሁሉ በክርክር ላይ የተመሠረተ ሳይሆን በአመራር ሰጭና በአመራር ተቀባይ መካከል ዘላቂ ሰላም ሰፍኖ የቤተ ክርስቲያኒቱ ሥራ በጋራ መከናወን እንዳለበት እናምናለን በማለት ከላይ የተገለፀውን መመሪያ በማጠናከር ሁሉም ከየተመደበለት የሥራ ዘርፍ ሳይወጣ ድርሻውን ያበረክት ዘንድ አመራርን ሰጥተዋል ፡፡

ከክቡራን ሚኒስትሮች አመራርና ማስጠንቀቂያ ባሻገር ጉባኤው በአንዳንድ የማኅበረ ቅዱሳን አባባል ላይ ውይይቱን በመቀጠል የነጥቦቹን ኃይለ ቃል መርምሮአል፡፡

ከማኅበረ ቅዱሳን አባላት የቀረበው ሪፖርት እንደሚያስረዳው ማኅበሩ የቅርብ ተጠሪ ከሆነው ከማደራጃ መምሪያው ኃላፊ ጋር በተፈጠረው የሥራ አለመግባባት ችግር ምክንያት ግንኙነቱን በቀጥታ ከጠቅላይ ቤተ ክህነትና ከዚያ በላይ ከሆኑት አካላት ጋር በማድረግ ሲሠራ መቆየቱን ያመለክታል ፡፡

የጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት እንዲህ ዓይነቱ የመዋቅር መጣስ ችግር ሲያጋጥመው የግራ ቀኙን ጥያቄ በማዳመጥና በቤተ ክርስቲያኒቱ መመሪያዎች በመታገዝ ወዲያውኑ ችግሩን ማስተካከል ሲገባው አላደረገም ፡፡ ይህን ባለማድረጉ የአሠራር ስህተት ተፈጽሟል ፡፡

ስለዚህ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤትም ሆነ ማኅበረ ቅዱሳን የተሰጣቸውን መመሪያ በመተላለፍ የፈጸሙትን የአሠራር ስህተት ማስተካከል ይጠበቅባቸዋል ፡፡

ከማኅበረ ቅዱሳን አባላት አንደበት የተደመጠው ሌላው ጉዳይ የሀገሪቱንም ሆነ የቤተ ክርስቲያኒቱን የፖለቲካ መስመር በሚነካ መልኩ የወጣ መጽሔትም ሆነ ጋዜጣ አለመኖሩን ነው ፡፡

የማኅበረ ቅዱሳን አባላት የእምነት ክህደት ቃል ተጠይቀው ፖለቲካዊ ሒደት የሚታይበትን ጽሑፍ ማዘጋጀታቸውን የሚያስተባብል ቃል ቢያስመዘግቡም በየጊዜያቱ የወጡት ጋዜጦችና መጽሔቶች በአስረጅነት ለጉባኤው ቀርበው ያረጋገጡባቸው ስለሆነ፤

ወደፊት በተጠሪው መሥሪያ ቤት በኩል ሳይመረመሩ ጋዜጦች መጽሔቶችና ሌሎች መሰል ጽሑፎች እንዳይወጡ የተሰጠውን መመሪያ ጉባኤው ተቀብሎታል ።

ሌላው ሳይጠቀስ የማይታለፈው ማኅበሩ ለቅዱስ ፓትርያርኩ ያለው አቋም የማያወላውል እንደሆነ ገልጾ፤ በቤተ ክህነት መሥሪያ ቤት ኋላቀር የሆነ አሠራር መሻሻል እንዳለበት የሚያስገነዝብ ቃለመጠይቅ አቅርቧል ።

ይህን ጥያቄ ለመመለስ የቅዱስ ፓትርያርኩን የዐሥራ ሰባት ዓመታት ጉዞን መፈተሽ ያስፈልጋል፤ የዐሥራ ሰባቱን ዓመታት የሥራ ጉዞ በመከተል ታይተው የማይታወቁ የተለያዩ የልማት ፕሮጀክቶች እየተዘጋጁ ከማዕከል እስከ አህጉረ ስብከት ከዚያም እስከጠረፍ ዳርቻ ባሉት የኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት መዋቅር ከፍተኛ ድርሻ የሚጠበቅባቸው የመሠረተ ልማት አገልግሎቶች ተዘርግተዋል ።

<u>ለማስረጃም ያህል</u>

1ኛ. በመንፈሳዊና ዘመናዊ ትምህርት ቤቶች አደረጃጀት፤
2ኛ. በከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና በኮሌጆች አወቃቀር፤
3ኛ. በካህናት ማሠልጠኛ ተቋማት አደረጃጀት፤
4ኛ. በመምህራንና ደቀ መዛሙርት እንክብካቤ፤
5ኛ. በቅዱሳት መጻሕፍት ኅትመትና ስርጭት፤
6ኛ. በቤተ መጻሕፍትና ሙዝየም አደረጃጀት፤
7ኛ. በሕፃናት እንክብካቤና በእናቶች ማቋቋም ተግባር፤
8ኛ. በሕንፃ አብያተ ክርስቲያናት ግንባታ፤
9ኛ. የቤተ ክርስቲያኒቱን ሀብትና ንብረት አመላለስ በተመለከተ እየተደረገ ባለው የመብት ማስከበር ስኬት፤
10ኛ. በቤተ ክርስቲያኒቱ ምጣኔ ሀብት አሰባሰብና በጀት አመዳደብ የተገኘው ብቃት፤
11ኛ. የሠራተኞች ደመወዝ ዕድገት ጥያቄ በአወንታ ይስተናገድ ዘንድ የአዲስ እስኬል ተዘጋጅቶ መውጣት፤
12ኛ. በውጭ ግንኙነት መምሪያ ዘርፍ እየተካሔደ ያለው የቤተ ክርስቲያናችን የዓለም ዕውቅና መስፋፋትና መጠናከር፤
13ኛ. በገጠር በከተማ የታየውና የሚታየው የሐዋርያዊ አገልግሎት መስፋፋትና መጠናከር፤
14ኛ. ኤች. አይ. ቪ. ኤድስን አስመልክቶ እየተሰጠ ባለው አመራርና እየተደረገ ባለው እርዳታ የተገኘው አመርቂ ውጤት፤
15ኛ. በተለይም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት ፕሬዚዳንትነት ዕድገት መብቃት የሚሉትና የመሳሰሉት ሁሉ በዋናነት ከሚጠቀሱት መካከል ጥቂቶቹ ናቸው ።

የቅዱስ ወቅዱስ ፓትርያርክ ልዩ ጽሕፈት
መዝገብ ቤት Archive
Patriarchate Private Secretariat

የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት

ከፍ ብሎ እንደተመለከተው ቤተ ክርስቲያኒቱ ያደረገችውና እያደረገች ያለው አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴ እስከ ቅርብ ዓመታት ድረስ ከቆየው የኋላ ቀርነቱ አሠራር ተላቆ በመደበኛውና በየአጋጣሚው የሚደረግ ስብሰባ ላይ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር

ሊቃውንት በተዘጋጀ ሪፖርት የተረጋገጠ ስለሆነ የተሠራው ሥራ ሁሉ እንደማኅበረ ቅዱሳን አባባል አናሳ ትኩት ሊሰጠው የሚገባ አይደለም ።

ሐቁ ከዚህ በላይ የተገለፀው ሆኖ እያለ የኒሳቀርነቱ ብሒል በየትኛው የሥራ ክፍል ሊንጸባረቅ እንደቻለ ቃለመጠየቁ አያብራራም ።

ዘርፈ ብዙ ችግሮችን ለማስወገድ ሰላምና ፍቅር የሚሰጠውን ጠቀሜታ ለማጎልበት አንድነትና ኅብረት የወሳኝነት ሚና አለው ። ተቻችሎ መሥራትና ተከባብሮ መኖር ከቤተ ክርስቲያኒቱ የአመራር መርሆዎች መካከል ተቀዳሚውን አጀንዳ ይዞ የሚገኝ ስለሆነ ታጋሽና ልበ ሰፊ ሆኖ መሥራት ብሩህ ተስፋን የሚያስገኝ ውጤት እንጂ ጠባብ አመለካከትን የሚያሰተናግድ ተልእኮ የለውም ።

ከዚህ አንፃር በድርጅቶቻችን ማለትም በመመሪያ ሰጭው በሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያና በመመሪያ ተቀባዩ በማኅበረ ቅዱሳን መካከል የተከሰተው የሥራ አለመግባባት ችግር ለዚህ ከፍተኛ የሰላም ጉባኤ ቀርቦ ሰፊና ጥልቅ ውይይት ከተደረገበት በኋላ ማኅበረ ቅዱን ከተፈቀደለት መተዳደሪያ ደንብ ሳይወጣ ከማደራጃ መምሪያው የሚተላለፍለትን መመሪያ እየተቀበለ ይሠራ ዘንድ የሚከተለውን መመሪያ ሰጥተናል ።

## መመሪያ

የቤተ ክርስቲያናችን የሥራ ዘርፍ በሆነው በሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያና በሥሩ በሚንቀሳቀሰው በማኅበረ ቅዱሳን ማኅበር መካከል በሚታየው አንዳንድ የሥራ አፈጻጸም ግድፈት ለመወያየትና ዘላቂ መፍትሔን ለማምጣት ዛሬ በተደረገው የሰላም ውይይትና ምክክር ብዙ ጠቃሚ ጉዳዮችን ለማየት ችለናል።

ማኅበሩ ስለነበረው አጠቃላይ ሥራና እንቅስቃሴም በሰፊው ተብራርቶአል ።

ይሁንና ከዚሁ ከተገነዘብነው አንጻር የማኅበሩ ቀጣይ እንቅስቃሴ ምን መምሰል እንዳለበት የመፍትሔ መመሪያዎች ማስቀመጡ በጣም አስፈላጊ ይሆናል።

ማኅበሩ ለቤተ ክርስቲያን ሃይማኖታዊ ድጋፍ ለመስጠት የተቋቋመ እንደመሆኑ መጠን በሥራው ሁሉ መሰናከል እንዳያጋጥመው መጠበቅ ከቤተ ክርስቲያን ይጠበቃል።

ከዚህ አንጻር ማኅበሩ በቀጣይ የሥራ እንቅስቃሴው የሚከተለውን ጠብቆ እንዲሠራ ያስፈልጋል፤

1. ማኅበሩ ከዛሬ ጀምሮ ግንኙነቱ በመተዳደሪያ ደምቡ መሠረት ከሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ጋር ብቻ ይሆናል፤ ከመምሪያው ዕውቅና ውጪ የሚፈጸመው ከሦስተኛ ወገን ጋር ግንኙነት ሕገ ወጥ መሆኑን እንዲገነዘብ፤

2. የቤተ ክርስቲያኒቱን የፋይናንስ አስተዳደር ማበልጸግ የሚቻለው፤ ገቢውንና ወጭውንም በትክክል እየተቆጣጠሩ መሥራትና ማሠራት የሚቻለው የሥራ

ዘርፉ ያሉት የባለድርሻ አካላት በማዕከላዊው አስተዳደር በታተመና አንድ ወጥ በሆነ የገቢና የወጭ ካርኒ መሥራት ሲችሉ እንደሆነ ይታመናል ፡፡

Patriarchate Private Secretariat

ከዚህ አንፃር የማኅበረ ቅዱሳን አባላት እንደሌሎቹ የቤተ ክርስቲያኒቱ መሥሪያ ቤቶች ሁሉ ጠቅላይ ቤተ ክህነት እያሳተመ በሚያሰራጫቸው የገቢና የወጭ ካርኒ እንዲሠሩ፤

3. ማኅበሩ ከመምሪያው በሚሰጠው መመሪያ መሠረት በእጁ የሚገኘው የሀብትና የንብረት እንቅስቃሴ ሁኔታ በዝርዝር ኦዲት እንዲደረግ፣ ጠቅላይ ቤተ ክህነቱም ከመምሪያው በሚቀርብለት ጥያቄ መሠረት ሕጋዊ ኦዲተር በመሰየምና በማቅረብ ሕጉ በሚፈቅደው መሠረት እንዲፈጽም፤

4. ከዚህ በፊት ከመተዳደርያ ደንቡ ድንጋጌ ውጭ የተደረገው በቤተ ክርስቲያን አስተዳደርና በፖለቲካ ጉዳዮች ጣልቃ የመግባት እንቅስቃሴ ከቤተክርስቲያኗ ፍላጎትና ከመተዳደሪያ ደንቡ ውጭ በመሆኑ ከዛሬ ጀምሮ ማኅበሩ በፖለቲካ ጉዳዮችና በቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ጣልቃ የመግባት አዝማሚያ ማቆም አለበት፤

5. የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት፣ የማደራጃ መምሪያውና ሌሎችም የቤተ ክርስቲያናችን ተቋማት የማኅበሩን መተዳደርያ ደንብ ማዕከል ባደረገ ሁኔታ ማኅበሩ ቤተ ክርስቲያንን ለማገልገል የሚያቀርብላቸውን ጥያቄ ሕጋዊ በሆነ መንገድ ማስተናገድ ይኖርባቸዋል፡፡

6. ዛሬ በስፋት የተገነዘብነው ነገር ቢኖር በሁሉም አቅጣጫ በቅዱስ ሲኖዶስ ጸድቆ በወጣው መተዳደሪያ ደንብ ያልተሠራ መሆኑን ነው፡፡ ስለዚህ ከዛሬ ጀምሮ ከመተዳደሪያ ደንቡ ውጭ መሥራትና መንቀሳቀስ ሕገ ወጥ መሆኑን ሁሉም ተገንዝቦ በመተዳደሪያ ደንቡ ብቻ እንዲሠራ ይህን መመሪያ አስተላልፈናል ፡፡

## ማጠቃለያ

ከፍ ብሎ በመግለጫውም ሆነ መግለጫውን መሠረት አድርጎ በወጣው መመሪያ የተገለፀው የውሳኔ ጽንሰ ሐሳብ ቀደም ሲል በመገናኛ ብዙኃን መተላለፉ የተረጋገጠ ስለሆነ፤ አሁንም ተጠናክሮ ይቀጥል ዘንድ ውሳኔው በሸኝ ደብዳቤ ሆኖ ለሚመለከታቸው ሁሉ እንዲተላለፍ ብለናል ፡፡

የመንበረ ፓትርያርክ